## የመጠበቅያ ጊዚያት

NHS ለእንክብካቤ የመጠበቅያ ጊዚያት አሉት፡፡ ይሁን እንጂ ታካሚዎች በጊዜውና ውጤታማ በሆነ መልኩ ህክምና ማግኘታቸው ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

በየእርስዎ GP በኩል ወደ ሌላ አገልግሎት ሪፈር ተብለው ከሆነ ለምን ሪፈር እንደተባሉ፣ የሚጠበቅ የመጠበቅያ ጊዜ፣ ቀጠሮን ለመጠበቅ ለመጠበቅ የእርስዎ ኃላፊነትና ባለ መገኘት ስለሚከተለው ውጤት ምክር ሊሰጥዎት ይገባል፡፡

## የተጨማሪ የጤና እንክብካቤ ወጪዎችን ድጋፍ

ኣብዛኛዎቹ የጤና እንክብካቤዎችና አገልግሎች በነጻ የሚሰጡ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በስኮትላንድ የተወሰኑ የNHS ታካሚዎች ለጥርስ እንክብካቤ፣ መነጽር፣ የዓይን ሌንስ፣ ሰው ሰራሽ ጸጉርና የስፌት መሳርያዎች እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ፡፡

ማንኛውም ዝቅተኛ ገቢ ያለው የ NHS ታካሚ ከተጨማሪ ክፍያዎቹ ነጻ ለመሆን በGP ተግባራት፣ NHS ሆስፒታሎች፣ መድኃኒት ቤቶችና የአገልግሎት ኤጀንሲዎች የሚገኙ የ HC1 ቅጽ በመሙላት መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ተቀባይነት ካገኙ የ HC2 የምስክር ወረቀት ይሰጥዊታል፡፡ ታካሚዎች ተጨማሪውን ክፍያ እንዲከፍሉ ሲጠየቁ የ HC2 የምስክር ወረቀትን ማቅረብ አለባቸው፡፡

## አስተያየቶችና ቅሬታዎች

የሚያቀርቡት ቅሬታ:

- በNHS ያገኙት ወይም እያገኙት ያለው እንክብካቤ
- በታዩበት ቦታ ያለ የሆነ ነገር፣ ለምሳሌ የዶክተሮች ቀዶ ጥገና፣ ሆስፒታል ወይም አምቡላንስ
- ማንኛውም በእርስዎ ህክምና የተሳተፈ የNHS ሰራተኛ
- በአካቢዎ አገልግሎቶቻችን የሚቀናጁበት መንገድ በህክምናዎ ወይ እንክብካቤዎ ሂደት ላይ ጉዳት አድርሶ ከሆነ

## ቅሬታ እንዴት ይቀርባል

መጀመርያ በህክምናው ለተሳተፈ ሰራተኛ ማናጋር አለብዎት፡፡ ይህንን ካደረጉ ቅሬታዎ ከመነሻው መለየት እንችላለን፡፡ በህክምናው የተሳተፈውን ሰራተኛ ማናገር ካልፈለጉ ከሱ በላይ ለሆነ የሰራተኛ አባል ይጠይቁ፡፡

አሁንም ደስተኛ ካልሆነ የግድ በጽሁፍ የሚቀርብ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ የሚፈልጉ ከሆነ ቅሬታዎን በጽሁፍ እንዲያቀርቡ እንረዳዎታለን:

- ሙሉ ስምዎትና አድራሻ (እንዲሁም የታካሚ ስምና አድራሻ ለእነርሱ ቅሬታ እየቀረቡ ከሆነ)
- በተቻለ መጠን መቼና ምን እደተፈጠረ በቂ መረጃ መስጠት አለብዎት፡፡

ቅሬታን እንዴት እንደሚቀርቡ ምክር ለማግኘት ወይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በሚከተለው አድራሻ ይግኙ:-

ስልክ ቁጥር: 0141 201 4500

ኢመይል: complaints@ggc.scot.nhs.uk

NHS Greater Glasgow and Clyde

# በስኮትላንድ የጥገኝነት ጠያቂዎችና ስደተኞች የ NHS አገልግሎት አጭር መመርያ (AHBT)

## በሚከተሉት ቋንቋዎች ይገኛል

ኩርድሽ፣ ፋርስ፣ አረብኛ፣ ትግርኛ፣ ማንድሪን፣ ፈረንሳይኛ፣ ኡርዱ፣ አማርኛ

## የስኮትላንድ ብሄራዊ የጤና አግልግሎት ('NHS')

የስኮትላንድ አገራዊ የጤና አገልግሎት ለሁሉም ጥገኝነት ጠያቂዎችና ስደተኞች በነጻ ይሰጣል፡፡

ማንኛውም ለጥገኝነት ያመለከተ በሂደት ላይ ያለ ይሁን ያልተሳካለት ሰው በስኮትላንድ እስከቆየ ድረስ የUK ዜግነት እንዳለው ሰው እኩል እንክብካቤው የማግኘት ዕድል አለው፡፡

በስኮትላንድ የጤና አገልግሎት በአጠቃላይ ሓኪሞች (GPs) ይሰጣል፡፡ ስለዚህ በ GP አገልግሎት መመዝገብ ይገባል፡፡

## በGP የጤና አገልግሎት ማግኘትና መመዝገብ

1. ከ NHS በመጡ የጥገኝነት ጤና አገናኝ ቡድን አባላት በሆኑ የጤና እንክብካቤ ባለሙያዎች የሚፈጸመው የጤና ምርመራ ለማግኘት የመነሻ አቅርቦቶች ሲቀርብልዎት፣ ይህ ምርመራ የጤና ሁኔታዊችን ለመለየትና ከ NHS አገልግሎት ለማገናኘት የሚደረግ ነው፡፡
2. ቡዱኑ የድሮና የቆየ አስመልክቶ መረጃ ያሳባስባል፣ ይህ ወደ አዲስ አቅርቦትዎ ወደ ቀረበው የ GP ይተላለፋል፡፡
3. በአዲስ አቅርቦት ውስጥ ሲሆኑ በአከባቢዎ ስለሚገኝ GP የሚገልጽ ካርድ ከNHS ይላክልዎታል፡፡ ለመመዝገብ ካርዱንና ሌላ GP አገልግሎት ለማግኘት የሚረዳዎትን ሌላ መለያ ይውሰዱ፡፡
4. የ GP ወይ የግባር ነርስ ተጨማሪ የጤና ምርመራ ሊሰጥዎት ይፈልጋል፡፡
5. ስለ አካባቢዊ የጥርስ ሃኪሞችና ኦፕቲሽያንስ መረጃ ያገኛሉ፡፡

## የጤና እንክብካቤ አካሄድ

### የሚደጋገም የጤና ጉዳይ ካልዎት

በጤና ሁኔታዎ ተመስርተው የእርሰዎ GP ከሚከተሉት አንዱ ደርጋል:

- ተጨማሪ ድርጊት የማያስፈልገው በእርስዎ ሁኔታ ላይ ያተኩራል
- ለመድሃኒት የሚሆን መገለጫ ይሰጣል፡፡
- ወደ ስፔሻሊስት አገልግሎት ሪፈር ይልዎታል (የእርስዎ GP እንደ የአእምሮ ጤና፣ ኦርቶፔዲክስ፣ ሳይሲቶራፒ እና ፖዲታሪ ያሉ አገልግሎቶች የሚያገናኝ ነው)
- ወደ ሆስፒታል ያስገባዎታል

የGP አግልግሎት ዝግ ሆኖ ዶክተርዎን ማናገር ካልፈለጉ በነጻ መስመር NHS 24 በ111 በመደወል ማናገር ይችላሉ፡፡

### ከባድ ህመም ወይም ጉዳት ቢኖርብዎት

በአካባቢዎ ወደ ሚገኘው የአደጋና አስቸኳይ ይሂዱ፡፡ ወደ አዲስ አቅርቦት ሲሄዱ የሚቀርብዎትን ይፈልጉ፡፡

### በአስቸኳይ

በ999 ይደውሉ

### ለNHS አግልግሎት ትርጉም ማግኘት

የሆስፒታል እና የ GP ቀጠሮዎችን፣ የጠርስ፣ የዓይን ሓኪም፣ የእግር ሓኪሞች ፋርማሲስትስ ጨምሮ ለ ሁሉም የ NHS አገልግሎቶች ተርጓሚ የማግኘት ዕድል አልዎት፡፡ የሰራተኛው አባል ለእርስዎ ተርጓሚ እንደሚጣ ቀጠሮ ይያዛል፡፡

## በቀጥታ የሚያገኝዋቸው የእርስዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች

### GPs

A GP የቤተሰብ ዶክተር ሲሆኑ ለNHS ታካሚዎች አጠቃላይ የጤና እንክብካቤ ዋናው የግንኙነት አካል ነው፡፡ ታካሚዎች ጤንነታቸውን እንዲጠብቁና ከህመም መከላከል ያደርጋሉ፡፡ በአጠቃላይ ህክምና የሰለጠኑ ናቸው፡፡

### የፋርማሲ ባለሙያዎች

የፋርማሲ ባለሙያዎች አከባቢዎችና በትላልቅ መንገ ሱቆች ይገኛሉ፡፡ በህክምና ጉዳዮች ምክር ሊለግስዎትና ለጥቃቅን ህመሞች ላይ ሊረድዎት ይችላሉ፡፡

### የጥርስ ሓኪሞች

በNHS በጥርስ ታካሚነት ለመመዝገብ በአከባቢዎ የሚገኘውን የጥርስ ህክምና ባለሙያን አግኝተው በNHS ለመመዝገብ ይጠይቁት፡፡ የጥርስ ህክምና ባለሙያዎ የአፍዎ፣ ጥርስዎና የድድዎ ንክብካቤውና ምክር ይሰጥዎታል፡፡

### የዓይን ሓኪም

ኦፐትሽያንስ በስኮትላንድ ለሚኖሩ ሁሉም UK ነዋሪዎች ነጻ የ NHS ምርመራዎችን የሚሰጡ ናቸው፡፡